# የገቢዎች ሚኒስቴር

## የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤትን

## አሠራር ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 178/2013

የካቲት 2012
አዲስ አበባ

# የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤትን አሠራር ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 178/2013

ታክስ ከፋዮች በታክስ ውሳኔ ላይ ያላቸውን ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉበት ተደራሽነት ያለው፣ በአግባቡ የተደራጀ፣ የተቀላጠፈና ፍትሃዊ የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርብ የታክስ የቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት በማደራጀት የታክስ ከፋዮችን ቅሬታ ለመፍታት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታዎች የሚታዩበትን የቅሬታ አቀራረብና ምርመራ እንዲሁም የውሳኔ ሃሳብ አቀራረብና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት እና የቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ማሻሻል በማስፈለጉ እንዲሁም በሚንስትር መ/ቤቱ ከተደረገው ተቋማዊ የአደረጃጀት ለውጥ ጋር የተጣጣመ የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤትን ለማደራጀትና አሠራሩን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 178/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፦

   1) "ሚኒስቴር" ማለት ገቢዎች ሚኒስቴር ነው፤
   2) "ጽ/ቤት" ማለት በሚኒስቴሩ ዋና መ/ቤት እንዲሁም በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአዋጁ አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚደራጅ የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ነው፤
   3) "አዋጅ" ማለት የፌዴራል የታክስ አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ሲሆን አዋጁን ለማስፈፀም የወጣውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 407/2009 ይጨምራል፡፡
   4) "የበላይ ኃላፊ" ማለት እንደሁኔታው ሚኒስትር ወይም በእርሳቸው የተወከለ የዘርፍ ኃላፊ ወይም የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡

5) በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቃላትና ሀረጐች በታክስ ህግ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በፌዴራል የታክስ አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 983/2008 መሠረት የታክስ ውሳኔዎችን በመቃወም በሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤትን ስለማደራጀት</u>

4. <u>የቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አደረጃጀት</u>

1/ በታክስ ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን አጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች ይደራጃል፡፡

2/ በዋናው መ/ቤትና በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች ሥር የሚደራጀው የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት እንደአስፈላጊነቱ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቡድኖች እንዲኖሩት ሊደረግ ይችላል፡፡

3/ ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ ቅ/ጽ/ቤቶች በእያንዳንዱ የታክስ ቅ/ጽ/ቤት የሚደራጀው የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አንድ የታክስ ቅሬታ አጣሪ ቡድን ይኖረዋል፡፡

4/ የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የሰው ኃይል በተቋሙ የመዋቅር ጥናት መሠረት የተወሰነው ይሆናል፡፡

5. <u>የታክስ ቅሬታ አጣሪ ቡድን ሰብሳቢዎች አሰያየም</u>

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4/2/ መሠረት በዋናው መ/ቤት እና በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች ሁለት የታክስ የቅሬታ አጣሪ ቡድኖች የሚደራጁ ከሆነ እንደሁኔታው የታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ ኃላፊ ወይም የቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ የሁለተኛውን ቡድን ሰብሳቢ ይሰይማሉ፡፡

6. <u>ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ ያሉ ቅ/ጽ/ቤቶች የታክስ ቅሬታ አጣሪ ሰብሳቢ</u>

ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ ባሉ ቅ/ጽ/ቤቶች የሚደራጀው የታክስ ቅሬታ አጣሪ ቡድን በጽ/ቤት ኃላፊው ሰብሳቢነት ይመራል፡፡

7. <u>የጽ/ቤቶቹ ተጠሪነት</u>፣

1) በዋና መሥሪያ ቤት የሚቋቋመው የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለሚኒስትር ወይም በሚኒስትሩ ለተወከለ ኃላፊ ይሆናል፣

2) በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚቋቋመው የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ይሆናል፣

3) የቅ/ጽ/ቤት ታክስ አጣሪ ጽ/ቤት ለዋናው መ/ቤት የታክስ አጣሪ ጽ/ቤት ስለሥራው በየጊዜው ሪፖርት ማድረግ አለበት።

8. <u>የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ሠራተኞች አመዳደብ</u>፣

1) የጽ/ቤቱ ሠራተኞች በዋናው መ/ቤት በሚንስትር እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሥራ አስኪያጁ የሚመደቡ ይሆናል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ሚኒስቴር መስርያ ቤቱ ወይም ቅ/ጽ/ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ባለሞያዎችን በቅጥር ወይም በደረጃ እድገት አወዳድሮ ሊመድብ ይችላል፣

3) በጽ/ቤቱ የተመደቡ ሠራተኞች ወይም የጽ/ቤቱ ኃላፊ ከአቅም በላይ በሆነ አስገዳጅ ምክንያት በሥራ ቦታ በማይገኙበት ጊዜ የታክስ ኦፐሬሽን ዘርፍ ኃላፊ ወይም የቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ በጊዜያዊነት ለጽ/ቤቱ የጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ሊመድብ ይችላል፤

4) የሚመደቡ ባለሞያዎች በተቻለ መጠን በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኦዲት፣ በአወሳሰን እና በህግ ሙያዎች ያገለገሉ መሆን አለባቸው።

5) የጽ/ቤት ሠራተኞችንና ባለሙያዎችን እንዲሁም የጽ/ቤት ኃላፊውን ዝውውር፣ ምደባ እና የደረጃ ዕድገት በሚመለከት የመ/ቤቱ አግባብነት ያላቸው መመሪያዎች እና የአደረጃጀት ጥናቶች ተፈፃሚ ይደረጋሉ።

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

9. <u>የጽ/ቤቱ ሥልጣን</u>

1) በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ታክስ ከፋይ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በሃያ አንድ ቀናት ውስጥ በውሳኔው ላይ በጽሑፍ የሚያቀርበውን የቅሬታ ማመልከቻና ደጋፊ ሰነዶችን ተቀብሎ በመመርመር የውሳኔ ሐሳብ ለሚኒስትር ወይም ሚኒስትሩ ለወከለው የበላይ ኃላፊ ያቀርባል።

2) ጽ/ቤቱ ታክስ ከፋዩ ያቀረበው ቅሬታ የታክስ ውሳኔውን የሚቃወምበት ምክንያትና የሚጠይቀውን ዳኝነት የሚገልጽ መሆኑን በማረጋገጥ ቅሬታውን ይቀበላል።

10. <u>የዋናው መሥሪያ ቤት የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ሥልጣን፤</u>

1/ የዋናው መ/ቤት የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ቅሬታ አቅራቢው፤

ሀ) የፌዴራል ከፍተኛ ግብር ከፋይ ከሆነ የተወሰነበት እና ለቅሬታ መነሻ የሆነው የግብር እና ታክስ መጠን ወለድ እና መቀጫን ጨምሮ ከብር 300,000,000 (ሦስት መቶ ሚሊየን) በላይ ከሆነ፣

ለ) የፌዴራል መካከለኛ ግብር ከፋይ ከሆነ የተወሰነበት እና ለቅሬታ መነሻ የሆነው የግብር እና ታክስ መጠን ወለድ እና መቀጫን ጨምሮ ከብር 200,000,000 (ሁለት መቶ ሚሊየን) በላይ ከሆነ፤

ሐ) የፌዴራል አነስተኛ ቅ/ጽ/ቤት ግብር ከፋይ ከሆነ የተወሰነበት እና ለቅሬታ መነሻ የሆነው የግብር እና ታክስ መጠን ወለድና መቀጫን ጨምሮ ከብር 100,000,000 (አንድ መቶ ሚሊየን) በላይ ከሆነ ቅሬታውን ተቀብሎ በመመርመር የውሳኔ ሐሳቡን ያቀርባል፡፡

2) ታክስ ከፋዩ ቅሬታ ባቀረበበት የታክስ ውሳኔ ላይ ያመነው ካለ በቅድሚያ ያመነበትን ታክስ በመክፈል ማስረጃውን ማያያዝ አለበት፡፡

3/ የዋናው መ/ቤት የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የቅ/ጽ/ቤት የታክስ አጣሪ ጽ/ቤቶችን ይደግፋል ይከታተላል፡፡

4/ የዋናው መ/ቤት የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት በሁሉም የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤቶች ተፈጻሚነት የሚኖረው ዝርዝር የአሠራር መመሪያ ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 በተደረነገገው መሠረት ጽ/ቤቱ የሚያወጣው ዝርዝር የአሠራር መመሪያ በታክስ ኦፐሬሽን ዘርፍ ሲፀድቅ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

11. <u>የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ሥልጣን፤</u>

የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት በዚህ መመሪያ አንቀጽ (12) ለዋናው መሥሪያ ቤት ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ከተሰጡት ሥልጣን በታች በሆኑ የታክስ ውሳኔዎች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ተቀብሎ በመመርመር የውሳኔ ሀሳብ ለሥራ አስኪያጁ ያቀርባል፡፡

12. <u>የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት፤</u>

1) የጽ/ቤት ኃላፊ የጽ/ቤቱን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ባለሙያዎችን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ጽ/ቤቱ በሰው ኃይል እና በቁሳቁስ እንዲሟላ ያደርጋል፤

Ethiopian Records &

2) ጽ/ቤቱ በሚያደርገው የቅሬታ ማጣራት ሂደት ከቅሬታው ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎችና ማስረጃዎች ከሚመለከታቸው አካላት እንዲቀርቡለት ትዕዛዝ ይሰጣል፤ የተያዘው ጉዳይ የህግ ወይም የሙያ ማብራሪያ የሚያስፈልገው ከሆነ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ያደርጋል፤

3) በማጣራት ሂደት ላይ የሚገኙ ጉዳዮችን በሚመለከት ወይም ከታክስ አወሳሰን ጋር በቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ግንኙነት ያላቸውን ማናቸውንም አካላት በመጥራት መረጃ ይቀበላል፡፡

4) በጽ/ቤቱ ተጣርቶ የቀረበ የውሳኔ ሀሳብ በቃለ-ጉባኤ በማስደገፍ ለበላይ ኃላፊው ያቀርባል፤

5) የጽ/ቤቱን ባለሙያዎችና ሠራተኞች የሥራ አፈፃፀም ይመዝናል፣ የክፍሉን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለበላይ ኃላፊው እና ሪፖርቱ ሊደርሳቸው ለሚገቡ ሌሎች አካላት በወቅቱ እንዲላክ ያደርጋል፤

6) ለበላይ ኃላፊው ቀርቦ የተወሰነ ውሳኔ ለቅሬታ አቅራቢውና ቅሬታው ለሚመለከተው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም የሥራ ሂደት እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት በሙሉ እንዲደርሳቸው ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን በመከታተል ውሣኔው ተፈፃሚ እንዲሆን ያደርጋል፣

7) የጽ/ቤቱ ሠራተኞች በማናቸውም ምክንያት ሲጓደሉ አዲስ እንዲመደብ ለሚመለከተው ኃላፊ ያሳውቃል፣

8) ለጽ/ቤቱ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በማደራጀት እና ጥናትና ትንተና በማድረግ የችግሩ መነሻና የመፍትሔ ሃሳብ ያካተተ ሪፖርት ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፣

9) የቅሬታ አቀባበልና አፈታትን ለማፋጠን የሚያስችሉ አሠራሮችንና የሥራ ማኑዋሎችን ከጽ/ቤቱ ባለሙያዎች ጋር በመሆን ይቀርፃል፤ ሌሎች ከጽ/ቤቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ ተግባራትን ያከናውናል፤

10) በመሥሪያ ቤቱ አደረጃጀት የተቀመጡትን የወል የሥራ ኃላፊነቶች ይወጣል፡፡

13. <u>የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የውሳኔ ሀሳብ አቀራረብ እና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት</u>፤

1) እያንዳንዱ የታክስ ቅሬታ በሚሰማበት ጊዜ ከክፍሉ አባላት ሁለት ሦስተኛው ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ እንደተሟላ ይቆጠራል፤

2) በተሟላ ምልዓተ-ጉባኤ በአብዛኛው የተደገፈው የውሳኔ ሃሳብ የቅሬታ አጣሪ ቡድኑ የውሳኔ ሀሳብ ይሆናል፡፡ ድምጽ እኩል የተከፈለ እንደሆነ በጽ/ቤት ኃላፊው የተደገፈው ሃሳብ የታክስ ቅሬታ አጣሪ ቡድኑ የውሳኔ ሀሳብ ይሆናል፡፡

3) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በውሳኔ አሰጣጡ ከአብዛኛው የተለየ ሀሳብ ያለው አባል የተለየበት የውሳኔ ሀሳብ በቃለ-ጉባኤ እንዲመዘገብለት ይደረጋል፡፡

4) የጽ/ቤቱ የውሳኔ ሀሳብ በቃለ-ጉባኤ ተመዝግቦ በውሳኔው የተስማሙ አባላት በፊርማ የሚያረጋግጡት ይሆናል፡፡

5) በቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤቱ የሚቀርበው የውሳኔ ሀሳብ በበላይ ኃላፊ ሲፀድቅ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡

14. <u>የታክስ ቅሬታ አጣሪ ቡድን የውሳኔ ሀሳብ</u>

1) የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 54 መሠረት፤

(ሀ) ቅሬታውንና የተደረገውን ክርክር፣

(ለ) ውሳኔ የሚስፈልጋቸውን ጭብጦች፣

(ሐ) ከውሳኔ ሐሳብ ላይ ለመድረስ ያስቻለውን ህግና ምክንያት እንዲሁም ማስረጃዎችን የያዘ መሆን አለበት፡፡

2) የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከማንኛውም ሰው ማንኛውንም ዓይነት ማስረጃ ወይም ማብራሪያ እንዲቀርብለት በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሐሳብ ከማቅረቡ በፊት የሚመለከተውን ሰው ወይም አካል ማዘዝ ይችላል፡፡

3) ከኦዲተሮች እንዲቀርቡ የሚፈለጉ ማብራሪያዎች ወይም የድጋሚ ኦዲት ሪፖርቶች ለጽ/ቤቱ መቅረብ ያለባቸው የቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የውሳኔ ሐሳብ ለበላይ ኃላፊው ከማቅረቡ በፊት መሆን አለበት፡፡

4) የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት በማንኛውም ሁኔታ ሌሎች የሥራ ክፍሎች ጽ/ቤቱ በያዘው ጉዳይ ላይ አጣርተው ውሳኔ እንዲሰጡ ጉዳዩን ማስተላለፍ አይችልም፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ስለማቅረብ</u>

15. <u>የታክስ ቅሬታ ስለማቅረብ፣</u>

ማንኛውም ታክስ ከፋይ በተወሰነበት የታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ (18) እና (19) የተመለከቱትን ግዴታዎች ካሟላ በታክስ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ማቅረብ ይችላል፤

16. <u>የታክስ ቅሬታ አቀራረብ፣</u>

1. የታክስ ቅሬታ አቅራቢው በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው የታክስ ውሳኔው በጽሑፍ በተሰጠው በሃያ አንድ ቀናት ውስጥ የቅሬታ ማመልከቻውን እንደ ሁኔታው ለዋናው መ/ቤት ወይም ለቅ/ጽ/ቤት ታክስ አጣሪ ጽ/ቤት ማቅረብ አለበት፤

2. ታክስ ከፋዩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ቅሬታውን ሳያቀርብ የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበት እንደሆነ በአዋጁ መሠረት በጽሁፍ ጥያቄ ለጽ/ቤቱ አቅርቦ በበላይ ኃላፊ ሲፈቀድ የጊዜ ማራዘሚያ ይሰጣል፡፡

17. <u>የታክስ የቅሬታ ማመልከቻ ይዘት፣</u>

1) ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የቅሬታ ማስታወቂያ የቅሬታውን ፍሬ ነገር እና ምክንያቶች መያዝ አለበት፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ቅሬታ አቅራቢው፤

(ሀ) የቅሬታ አቅራቢውን ስምና አድርሻ፣
(ለ) ቅሬታ የቀረበበትን የታክስ ውሳኔ ይዘት፣
(ሐ) ውሳኔው የተሰጠበትን ቀን፣
(መ) ውሳኔ የሰጠውን ቅ/ጽ/ቤት እና
(ሠ) ሌሎች ለውሳኔ የሚረዱ ፍሬ ነገሮችና ማስረጃዎችን መግለጽ አለበት፡

3) ቅሬታ አቅራቢው የንግድ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የምስክር ወረቀት፣ እንዲሁም ጉዳዩ በታክስ ወኪሉ የሚቀርብ ከሆነ ለወኪሉ ቅሬታ አቅራቢው ውክልና የሰጠበት ማስረጃ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ከሆነ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ አለበት፤

4) የቀረበውን ቅሬታ የሚያስረዱ አግባብ ያላቸው ሌሎች ኮፒ የሰነድ ማስረጃዎች ከዋናው ጋር እንዲገናዘቡ ከቅሬታ ማመልከቻቸው ጋር በአባሪነት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

18. <u>የታክስ ቅሬታ ማመልከቻ የሚቀርብበት ቀንና አቀራረብ፣</u>

1) የቅሬታ ማመልከቻ የቀረበበት ቀን የቅሬታ አጣሪ ቡድኑ የሪከርድ ሥራ አመራር ባለሙያ ፈርሞ የተቀበለበት ቀን ነው፤

2) የቅሬታ ማመልከቻ በቅሬታ አቅራቢው ወይም በሚወክለው የታክስ ወኪል ተፈርሞ መቅረብ አለበት፣

19. <u>በቅሬታ ላይ ውሳኔ የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ፤</u>

1) በታክስ ውሳኔ ላይ ታክስ ከፋዩ ላቀረበው ቅሬታ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ቅሬታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት አንድ መቶ ሰማንያ ቀናት ውስጥ ለቅሬታው ውሳኔ መስጠት አለበት፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ቅሬታ አጣሪው ውሳኔ ካልሰጠ ቅሬታ አቅራቢው የጊዜ ገደቡ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ማቅረብ ይችላል።

3) በቀረቡ ቅሬታዎች ላይ ጽ/ቤቱ ለተጨማሪ የማጣራት ሥራ የሚሰጠው የጊዜ ገደብ ቢባዛ ከአንድ ወር መብለጥ የለበትም፣

## <u>ክፍል አምስት</u>

20. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች</u>

1) የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የአሠራር መመርያ ቁጥር 127/2009 እና 165/2012 በዚህ መመሪያ ተሽረዋል።

2) ቀደም ሲል የነበሩ አሠራሮች ይህን መመሪያ የሚቃረኑ ከሆኑ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

21. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 እና 11 የተደነገገው ቢኖርም ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የቀረቡ እና ውሳኔ ያላገኙ ቅሬታዎች በዚህ መመሪያ መሠረት ውሳኔ እንዲያገኙ ይደረጋል።

22. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስትር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል።

አዲስ አበባ የካቲት 2012 ዓ.ም

አዳነች አቤቤ
የገቢዎች ሚኒስትር

# በታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አደረጃጀት እና አሠራር ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 165/2012 ላይ የተደረገ ማሻሻያ

| አንቀጽ | የድንጋጌው ይዘት | የተደረገ ማሻሻያ | ማሻሻል/ማስተካከል ያስፈለገበት ምክንያት |
|---|---|---|---|
| 2 /5/ | በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቃላትና ሀረጐች በታክስ ህግ የተሰጣቸውን | በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቃላትና ሀረጐች በታክስ ህግ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡ | ዓረፍተ ነገሩ ስላልተቋጨ ዕልባት ለመስጠት፤ |
| 4 /1/ | በታክስ ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን አጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት በዚህ መመሪያ መሠረት ይደራጃል፡፡ | በታክስ ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን አጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች ይደራጃል፡፡ | ጽ/ቤቱ በዋና መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች የሚደራጅ መሆኑን የማያሳይ ስለሆነ፤ |
| 4 /2/ | የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት እንደአስፈላጊነቱ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቡድኖች እንዲኖሩት ተደርጐ ሊደራጅ ይችላል፡፡ | በዋናው መ/ቤትና በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች ሥር የሚደራጀው የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት እንደአስፈላጊነቱ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቡድኖች እንዲኖሩት ሊደረግ ይችላል፡፡ | በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች ሁለት የቅሬታ አጣሪ ቡድን ሊያደራጁ እንደሚችሉ ከመመሪያው አንቀጽ 4 /3/ መገመት ቢቻልም በግልጽ ያልተደነገገ ስለሆነ፤ |
| 4 (4) | - | የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የሰው ኃይል በተቋሙ የመዋቅር ጥናት መሠረት የተወሰነው ይሆናል፡፡ | የጽ/ቤቱን የሰው ኃይል ለማሰማራት የተቋሙን የአደረጃጀት ሰነድ መጠቀም ተገቢ ስለሆነና አዲስ አንቀጽ ማካተት ስለሚገባ፤ |
| 5 /1/ | በዋናው መ/ቤት ሁለት የታክስ የቅሬታ አጣሪ ቡድኖች የሚደራጁ ከሆነ በጽ/ቤት ኃላፊው ሰብሳቢነት የሚመራ ይሆናል፡፡ | በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4/2/ መሠረት በዋናው መ/ቤት እና በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች ሁለት የታክስ የቅሬታ አጣሪ ቡድኖች የሚደራጁ ከሆነ እንደሁኔታው የታክስ ኦፐሬሽን ዘርፍ ኃላፊ ወይም የቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ የሁለተኛውን ቡድን ሰብሳቢ ይሰይማሉ፡፡ | በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሁለት ቡድን ማደራጀት እንደሚችሉ የሚፈለግ ቢሆንም በመመሪያው ስላልተገለጸ፤ የአንዱን ቡድን ሰብሳቢ የዘርፍ ኃላፊ ወይም ሥራ አስኪያጅ እንዲሰይሙ ለማድረግና ከአንቀጽ 4/2/ ጋር ለማስተሳሰር፤ |
| 6 | በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7(3) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በቅ/ጽ/ቤት የሚደራጀው የታክስ ቅሬታ አጣሪ ቡድን በጽ/ቤት ኃላፊው ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ፣<br>(ሀ) አንድ መሪ ባለሙያ<br>(ለ) ሦስት ከፍተኛ ባለሙያዎች<br>ይኖሩታል፡፡ | ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ ባሉ ቅ/ጽ/ቤቶች የሚደራጀው የታክስ ቅሬታ አጣሪ ቡድን በጽ/ቤት ኃላፊው ሰብሳቢነት ይመራል፡፡ | በአደረጃጀት ሰነድ መካተት ያለበት የባለሙያዎች ስብጥር ዝርዝር በመመሪያው ውስጥ መገለጹ በየጊዜው ከሚለዋወጠው መዋቅር አንፃር ለአሰራር ስላላመቸ ከመመሪያው እንዲወጣ ለማድረግና የአንቀጹን ርዕስ ለማስተካከል፤ |
| 8 /2/ | ሚኒስቴር መስርያ ቤቱ ወይም ቅ/ጽ/ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ባለሞያዎችን በቅጥር ወይም በደረጃ እድገት አወዳድሮ ሊመድብ ይችላል፣ | በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ሚኒስቴር መስርያ ቤቱ ወይም ቅ/ጽ/ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ባለሞያዎችን በቅጥር ወይም በደረጃ እድገት አወዳድሮ ሊመድብ ይችላል፣ | በንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ከተገለጸው ጋር የተገናዘበ እንዲሆን ለማድረግ፤ |